# “የካቲት 11 በመጣ ቁጥር እንጠየቃለን፣ መልስ ግን የለም”

**"የካቲት 11 በመጣ ቁጥር እንጠይቃለን፤ መልስ ግን የለም"**
የአ.አ ነዋሪ የትግራይ ተወላጆች
**"የአንበሳ ድርሻ ፈልጋችሁ ከሆነ ትግሉን ወደኋላ ትመልሱታላችሁ"**
ሰብሳቢዎች

በየማነ ናግሽ (ከኢትዮጵያ ሪፖርተር የተወሰደ)

የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም. ህወሓት የተመሰረተበት 34ኛ ዓመት አስመልክቶ በተደረገ ውይይት "የካቲት 11 በመጣ ቁጥር እንጠይቃለን፤ መልስ ግን የለም" ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ የትግራይ ተወላጅ ወጣቶች ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ከመድረክ ሰብሳቢዎች "የአንበሳ ድርሻ ፈልጋችሁ ከሆነ ትግሉን ወደኋላ ትመልሱታላችሁ" የሚል መልስ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ባለፈው ቅዳሜ በብሔራዊ ቲአትር በተካሄደ ውይይት ወጣቶቹ በርካታ ጥያቄዎችን አንስተዋል፡፡ በስፍራው ተገኝቶ ለመታዘብ እንደተቻለው ወጣቶቹ ጥያቄ ሲያቀርቡ በጭብጨባ ይታጀብ ነበር፡፡

ወጣቶቹ ካነሱዋቸው ጥያቄዎች መካከል፣ "ፍትህ የለም፣ ሰው አለአግባብ በፖሊስ ይደበደባል፣ ተራራ እያፈረሰ የሚውል ሕዝብ ተገቢ ዋጋ አይከፈለውም፣ ብልሹ አስተዳደርና ሙስና ሰፍኗል፣ በሌሎች አካባቢዎች የሚደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎች በክልሉ የሉም" ወዘተ የሚሉ ይገኙባቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ ስርዓቱን ከአፄ ኃይለሥላሴና ከደርግ ጋር ያነፃፀሩም አልጠፉም፡፡

"በትግራይ ሕዝብ መስዋዕትነት በመጣ ስርዓት የትግራይ ሕዝብ ተጠቃሚ አይደለም፡፡ አሁንም ጭቆና በሰፊው ይፈፀምበታል፣ ሰሚ አጥተናል" ወዘተ የሚሉ በርካታ ጥያቄዎች በቀረቡበት ወቅት የስብሰባ አዳራሹ በጭብጨባ ደምቋል፡፡ በተለይ አንዳንዶቹ እነዚህ ጥያቄዎች አምናም ካቻአምናም ያቀረብናቸው ቢሆንም መልስ ግን የለም፣ አሁንም እየጠየቅን ነው ብለዋል፡፡ ህወሓት የትግራይ ተወላጆች የሚፈልገንና የሚያነጋግረን ሲቸግረው ብቻ ነው፣ ችግራችንን ለመስማት አይሰበስበንም፣ ለራሱ ፖለቲካዊ ጥቅም ብቻ እንጂ የሚሉ ጥያቄዎችንም አቅርበዋል፡፡

የህወሓት/ኢህአዴግ የፓርላማ አባልና የመድረኩ ሰብሳቢ አቶ አታክልቲ ግደይ "ህወሓት ከኃይለሥላሴና ከደርግ ጋር የሚነፃፀር አይደለም፣ የመረጃ ክፍተት ስላለባችሁ ነው" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በማከልም "የምትሉት ነገር የትግራይ ሕዝብ ትልቅ መስዋዕትነት ስለከፈለ የተለየ ጥቅም ማግኘት አለበት ከሚል ኢ-ዴሞክራሲያዊ አመለካከት የመነጨ ነው" ብለዋል፡፡ "የአንበሳ ድርሻ ለመውሰድ ፈልጋችሁ ከሆነ ትግሉ ወደ ኋላ ትመልሱታላችሁ፤ አንድም እርምጃ መጓዝ አትችሉም" ብለዋል፡፡

አንዳንድ ወጣቶች ከስብሰባው በኋላ "ያቀረብነው ጥያቄ እና የተሰጠው ምላሽ ግንኙነት የለውም" በማለት ለሪፖርተር ጋዜጣ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ "እኛ የምንጠይቀው የትግራይ ሕዝብ እኩል ተጠቃሚ ይሁን የሚል ነው፡፡ ለ17 ዓመት የገዛ ድርጅት ለአንድ ዓመት የገዛም አይመስልም፡፡ ይህን ጥያቄ ህወሓት ማድበስበስ የለበትም" በማለት በምላሹ አለመርካታቸውን ገልፀዋል፡፡